# ጸሎተ ቅዳሴ

*በእደ ማርያም እጅጉ ረታ*

ቅዳሴ ማለት ምስጋና ሲሆን «ቀደሰ፣ አመሰገነ» ከሚለዉ የግእዝ ቋንቋ የተወሰደ ነው።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የማስተማር ተግባሩን ባጠናቀቀበት እና ወደ መስቀል እንደሚወሰድ በተናገረበት፣ የትህትናን ሥራ ሠርቶ ባሳየበት ዕለተ ሐሙስ ነገ ስለ እናንተ የሚቆረሰው ሥጋዬ ይህ ነዉ፤ ስለ እናንተ የሚፈሰው ደሜ ይህ ነዉ ሲል ለደቀመዛሙርቱ ሥርዓት ተከለላቸው። በዚህ ጊዜ የምስጋና ጸሎት እንደሚገባ አስተማራቸው። በማግስቱ በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ በኃጢአት የወደቀውን የሰውን ልጅ አዳነው። ይህም ሥርዐት ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ እየተፈጸመ ይገኛል ሐዋ. 2፣42።

ኢትዮጵያም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የኦሪቱ መስዋእት የተሰዋባት፣ በሐዲስ ኪዳንም አማናዊው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ በቤተ መቅደሱ እየተፈተተ እያንዳንዱ በንስሐ እየታጠበ የክርስቶስን አካል እንዲለብሱ ስትመክር ስትጋብዝ ስትፈጽም ቆይታለች፤ ወደፊትም እንዲሁ።

በኢትዮጵያም ይህ ታላቅ ሥርዓት ተጀመረ የሚባለው የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበረዉ ቅዱስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን ሊቀጳጳስ አድረጎ ሹሞ ከላከበት ካ4ኛው ክፍለ ዘመን (332 ዓ.ም) ጀምሮ ነዉ።

ፍሬምናጦስም ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸውን መጽሐፈ ቅዳሴ ይዞ እንደመጣ ይታወቃል። ምንም እንኩዋ በ4ኛዉ ክፍለ ዘመን በሀገራችን የግሪክ ቋንቋ እንደሚታወቅ ከታሪካዊ ሐውልቶች ላይ የሰፈረው ጽሑፍ ምስክር ቢሆንም ብዙሃኑ ሕዝብ የሚናገረው ባለመሆኑ ወደ ሀገራችን ቋንቋ እንዲተረጐም አስፈላጊ ነበር። ትክክለኛ የተተረጐመበትን ወቅት ለመናገር ባይቻልም በ5ኛዉ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ግድም ላይ ወደ ግዕዝ ለመተርጐሙ እርግጥ ነው። በአሁን ወቅት እየተገለገልንበት ያለው የቅዳሴው አሠራር (format) ፣ ቃላቱም ተመሳሳይነት ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን የተወሰደ ቢሆንም ቅድስና ከሙያ ብቃት ጋር የነበራቸው ኢትዮጵያን ሊቃውንት በየዘመናቱ አሻሽለው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ለማስባል ችለዋል።

ጸሎተ ቅዳሴ በሁለት ይከፈላል፤

1ኛ/ ሥርዓተ ቅዳሴ (Ordo Communis)
2ኛ/ ፍሬ ቅዳሴ (Anaphoras) በመባል ይታወቃል።

በመጀመሪያው ሥርዐተ ቅዳሴ (የመግቢያ ክፍል) ለካህኑ፣ ለዲያቆኑ፣ ለምእመናኑ፣ የድርሻው ጸሎት የተሠራለት ሲሆን ከሐዲስ ኪዳን መልክታት እና ግብረ ሓዋርያት (የሐዋርያት ሥራ)፣ ከተነበበ በኋላ የኪዳን ጸሎት እንደተፈጸመ ከመዝሙረ ዳዊት ለዕለቱ ተስማሚው ተመርጦ በዲያቆኑ ተሰብኮ ቅዱስ ወንጌል ይነበባል።

እስከዚህ ያለው ጸሎት አማኝም ሆነ የማያምን ለማመን የሚያዘጋጀው ትምህርት ስለሆነ ለመሳተፍ እንዲችል ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሠርታለች። ከዚህ በኋላ የክርሰቲያን ታናናሾች እንዲሰናበቱ በዲያቆኑ አዋጅ ይነገራል። ከዚያ አንስቶ የሃይማኖት ጸሎት በአንድነት እስከሚነበብበት ድረስ ለክርስትና ፣ ለጸሎተ ፍትሐት የሚደረግ ጸሎትን ያካትታል። መሪው ካህን ዕጽበተ እድ ይፈጽማል። በመቀጠልም በዲያቆኑ አማካኝነት ሁሉም እርስ በእርስ እጅ እንዲነሳሱ አዋጅ እስከሚናገርበት ያለው ክፍል 1 (ሥርዐተ ቅዳሴ) በመባል ሲታወቅ በሌሎችም ተመሳሳይ አብያተ ክርስቲያናትም የሚፈጸም ቢሆንም የእኛ ትንሽ ለየት ይላል።

በእኛ ቤተክርስቲያን የሁለተኛው ክፍል (ፍሬ ቅዳሴ) ብዛታቸው 20 ሲሆን ነገር ግን የምንገለገልባቸው 14 ናቸው። የሚታወቁት ፍሬ ቅዳሴዎች ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፤

1. የሐዋርያት ቅዳሴ
2. የጌታ ቅዳሴ
3. የዮሐንስ ወልደ ነጎድጉዋድ ቅዳሴ
4. የ318 ሊቃውንት ቅዳሴ
5. የእመቤታችን ቅዳሴ
6. የቅዱስ አትናቴዎስ ቅዳሴ
7. የቅዱስ ባስልዮስ ቅዳሴ
8. የቅዱስ ጎርጎርዮስ ቅዳሴ
9. የቅዱስ ኤጲፋንዮስ ቅዳሴ
10. የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴ
11. የቅዱስ ቄርሎስ ቅዳሴ
12. የቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ቅዳሴ
13. የቅዱስ ጎርጎርዮስ ቅዳሴ
14. የቅዱስ ዲዮስቆሮስ ቅዳሴ

ከዚህ በታች በየስማቸውና አርስታቸው የተዘረዘሩት በታላላቅ ገዳማት፣ አድባራት፣ ቤተመዘክር እንዳሉ ቢታወቅም በአንድ ጥራዝ ላይ ታትመው ለአገልግሎት ሲውሉ አይታዩም። ይህም ወደፊት ጥናታዊ ማብራሪያ ስለምንሰጥበት በዚሁ አልፈነዋል።

15. የእመቤታችን ቅዳሴ ቁጥር 2 (በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ)
16. የቅዱስ ማርቆስ ቅዳሴ
17. የቅዱስ ያዕቆብ ቅዳሴ (ሐዋርያዉ)
18. የእመቤታችን ቅዳሴ ቁጥር 3 (ጎርጎርዮስ)
19. የእመቤታችን ቅዳሴ ቁጥር 4 (ጎርጎርዮስ)
20. የቅዱስ ቄርሎስ ቅዳሴ (ቁጥር 2)

በፍሬ ቅዳሴ ብዛት ኦሪየንታል ከሚባሉት አብያት ክርስቲያናት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘችው የሶርያ ቤተክርስቲያን ስትሆን ኢትዮጵያ ሀገራችን በ2ኛ ደረጃ ትገኛለች።

ፍሬ ቅዳሴዎች የተጻፉበት ቅደም ተከተልና ጸሐፊዎቹ በእርግጠኛነት ለማወቅ ባይቻልም በቀደምትነት የሚታወቁት የሐዋርያት ቅዳሴ እና የጌታ ቅዳሴ ናቸው፤ (ቁጥር 1 እና 2) የቅዱስ ባስልዮስ ቅዳሴ (7) ከውጭ የተወሰዱ ለመሆናቸዉ ጥርጥር የለውም።

የተቀሩት ቅዳሴዎች ምንም እንኳን ደራሲዎቻቸው በሐዋርያት እና በቅዱሳን ስም ቢሆኑም የኢትዮጵያን አባቶቻችን ድርሰቶች እንደሆኑ የተደረጉት ጥናቶች ያመለክታሉ። የኢትዮጵያን አባቶቻችን ድርሰታቸው የራሳቸው መሆኑን ያልገለጹበት ምክኒያት ክብራቸዉ ይገለጥ ዘንድ ስለማይፈልጉና ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ጭምር ነው። አለበለዚያም ከውጭ የተገኙት ላይ መሠረት አደርገው አስፋፍተው የጻፉት ነው ምክኒያቱም በእነዚህ አንዳንድ አባቶች ስም የተጻፉት ቅዳሴዎች በሌሎች ሀገር ከሚገናኙት ጋር ሲነጻጸር ተመሳሳይነት የላቸውም።

ቅዳሴ የምስጋና ሁሉ ምደምደሚያ (ማሰሪያ) በመሆኑ እያንዳንዳችን በቤተክርስቲያን ተገኝተን የጸሎቱ ተሳታፊ በመሆን ለእኛ ኃጢአት በቀራንዮ የተሰቀለውን የክርስቶስን ሥጋውና ደሙን ልንቀበልና የክብሩ ወራሾች ልንሆን ይገባል። ሥጋውና ደሙ የሚፈተተዉ ለሕጻናትና ሽማግሎች ብቻ ሳይሆን ከ40 እና ከ80 ቀን ጀምሮከመንፈስ ቅዱስ ልጅነት ሳገኙ በሁሉም እድሜ ክልል ላሉ ነው።

ስለዚህ ለሠራነውን ኃጢአት ንስሐ እየገባን ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ጸሎተ ቅዳሴው ከመጀምሩ በፊት በቤተ ክርስቲያን በመገኘት በሥርዐተ ቅዳሴው እና በፍሬ ቅዳሴው የሚነበቡትን ምስጢራት ልናስተውል ልንረዳ ይገባል። በምናስቀድስበትም ጊዜ ከመሰቀሉ በፊት በዕለተ ሓሙስ የሠራልንን ሥርዐት እንዲሁም ለእኛ ለሰው ልጆች በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ ተሰቅሎ ሥጋውን የቆረሰልን፣ደሙን ያፈሰሰልንን መሆኑን እያሰብን የሠራነውንም ኃጢአት እንዲያስተሰርይልን ሊሆን ይገባል። ይህንንም እንፈጽም ዘንድ የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ከእኛ ጋር ይሁን።

ስለ ሥጋውና ደሙ ሥርዐት፣ እንዴት ልንቀበለው እንደሚገባን ምስጢረ ቊርባንን ይመልከቱ።

www.ethiopianorthodox.org

## <u>ዋቢ መጻሕፍት</u>

### መጽሐፈ ቅዳሴ


E. Hammerschmidt, Studies in the Ethiopic Anaphoras, Berlin 1961.

The Divine Liturgy According to the Rite of the Ethiopian Church, Paulos Tzadua

The Church of Ethiopia, A publication of the Ethiopian Orthodox Church , Addis Ababa, December 1970.


<u>January 2004</u>

www.ethiopianorthodox.org